02

5ኛ ዓመት ቁጥር 5th year N° 31	ባህር ዳር ህዳር 10 ቀን 1991 Bahir Dar, 19th Nov. 1998

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE
IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 2.40	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ	የፖ.ሣ.ቁ 312 P.o.BOX

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 31 / 1991
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ስለቴምብር ቀረጥ አከፋፈል የወጣ አዋጅ ገፅ 11

CONTENTS

Proclamation Nº 31 / 1998
A Proclamation To Provide For The Payment Of Stamp Duty Page 11

አዋጅ ቁጥር 31/ 1991

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ስለቴምብር ቀረጥ አከፋፈል የወጣ አዋጅ

በሰነዶች ላይ የተጣለው የቴምብር ቀረጥ የኪነጥበብ እድገትንና የካፒታል ንብረት ዝውውርን ለማገዝ በሚያስችል አኳኋን እንዲሻሻል ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፤

በአንዳንድ ሰነዶች ላይ የተጣለውን የቴምብር ቀረጥ ከሰነዱ ተጠቃሚዎች የመክፈል አቅም ጋር ማጣጣም በማስፈለጉ፤

ይህን ለማድረግም በፌዴራል ደረጃ የተቀረጸውን ማሻሻያ አዋጅ ከክልሉ ተጨባጭ

PROCLAMATION Nº 31 /1998

A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE PAYMENT OF STAMP DUTY

WHEREAS, it has become necessary to amend the stamp duty levied on documents in a manner which would contribute to the development of art, the activities of financial institutions and the transfer of capital assets;

WHEREAS, the stamp duty levied on some documents should consider the capacity of the users.

WHEREAS, it has become important to

ይህን ለማድረግም በፌዴራል ደረጃ የተቀረጸውን ማሻሻያ አዋጅ ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ማውጣት በማስፈለጉ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/9/ መሠረት የሚከተለውን አውጇል።

1/ <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የአማራ ብሔራዊ ክልል የቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 31/1991" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2/ <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

1. "ግልግል" ማለት ስለግልግል ፤ ስለ እርቅ፤ ስለ ስምምነት ወይም ስለሌላ ተመሣሣይ ጉዳይ በሁለት ተዋዋይ ወገኖች በተደረገ ስምምነት መሠረት በፍርድ ቤት ሳይሆን በገላጋዬች አልቆ በጽሑፍ የተሰጠ ውሣኔ ነው።

2. "ማገጃ" የተወሰነ ነገር በመፈጸሙ ወይም ባለመፈጸሙ ምክንያት የሚቀር ሆኖ አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበት ማናቸውንም ሰነድ ወይም በምስክር የተረጋገጠ ሆኖ ነገር ግን በትዕዛዝም ሆነ ለአምጪው የማይከፈልበት አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበትን ማናቸውንም ሰነድ ይጨምራል።

3. "የኅብረት ስምምነት" ማለት በአንድ ወይም ከአንድ በሚበልጡ የሠራተኞች ማኅበራት ወኪሎች እና በአንድ ወይም ከአንድ በሚበልጡ አሠሪዎች ወይም የአሰሪ ማኅበራት ወኪሎች ወይም አሰሪዎችን በሚወክሉ ተጠሪዎች መካከል ስለሥራ ሁኔታዎች የሚደረግ በጽሁፍ የሰፈረ ስምምነት ነው።

4. "የሥራ ውል" ማለት ማንኛውም ሰው ደመወዝ እየተከፈለው በአሰሪ መሪነት

capacity of the users.

WHEREAS, it has become important to proclaim harmonizing with the Federal Proclamation.

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 49(3) (9) of the Consitution of the Amhara National Regional State, it is hereby proclaimed as follows.

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Stamp Duty Proclamation N° 31/1998".

2. Definitions

In this proclamation, unless the context otherwise requires;

1. "Award" means a decision in writing rendered by an arbitrator(s) on a reference made otherwise than by order of court in the course of suit by parties to a compromise, conciliation or arbitral submission or other similar matters;
2. "Bond" includes any instrument, whereby a person obliges himself to pay money to another, on condition that the obligation shall be void, if a specific act is performed or is not performed, as the case may be; or any instrument attested to by a witness and not payable to order or bearer, whereby a person obliges himself to pay money to another;
3. "Collective Agreement" means an agreement concluded in writing between one or more representative of trade unions and one or more employers or agents or representatives of employers organizations;
4. "Elements of a Contract" means A contract of employment shall be

በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ሥራ ለአሰሪው ለመሥራት ሲስማማ በሁለቱ መካከል የሚመሠረት ውል ነው።

5. "ሰነድ" ማለት ማናቸውም መብት ወይም ግዴታ የተመሰረተበት የተመዘገበበት የተላለፈበት የተወገደበት ልኩ የተወሰነበት ወይም የተስፋፋበት ወይም የተጠቀሰው ድርጊት ተፈጽሟል የተባለበት ማንኛውም የጽሁፍ መረጃ ነው።

6. "ቢሮ" ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገንዘብ ቢሮ ነው።

7. "ማረጋገጫ" ማለት የሕዝብ ጉዳዮችን ለማረጋገጥ ስልጣን ባለው ሰው በሰነዶች ላይ የሚሰጥ ምስክርነት ነው።

8. "ሰው" ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ቢሆንም ባይሆንም ማናቸውም ድርጅት ነው።

9. "ሰነድ ማስፈጸም" ማለት ሰነድ መስራት፣ ማውጣት፣ በሰነዱ የተመለከተውን ማስፈጸም ወይም ሰነዱን ማዛወር ነው።

10. "የመያዣ ሰነድ" ማለት ተበዳሪው ወይመ ዋሱ ለአበዳሪው በሙሉ ወይም በከፊል ንብረቱን በመያዣነት የሚሰጥበት ሰነድ ነው።

11. "መተዳደሪያ ደንብ" እንደአግባብነቱ የመመስረቻ ጽሁፍን ይጨምራል።

3/ <u>የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልባቸው ሰነዶች</u>

የሚከተሉት ሰነዶች የቴምብር ቀረጥ ይከፈልባቸዋል።

1. የማንኛውም ንግድ ማኅበር፣ የኅብረት ሥራ ማኅበር ወይም የማንኛውም ዓይነት ማኅበር መመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ፣
2. ግልግል
3. ማገቻ

deemed formed where a person agrees directly or indirectly, to perform work for and under the authority of an employer for a definite or indefinite period or piece work in return for remuneration.

5. "Instrument" means a written document by which any right or obligation is or purports to be created, recorded, transfered, extinguished or by which its scope is limited or extended;

6. "Bureau" shall mean the Amhara National Regional State Finance Bureau.

7. "Notarial act" means an act of attestation and certification performed by person(s) authorized to perform such acts;

8. "Person" means any natural person or any organization irrespective of having juridical personality;

9. "To Execute Instrument" means to draw, issue, to carry into effect or to negotiate an instrument;

10. "Security deed" means any instrument where by a borrower or guarantor gives to a lender a charge upon a part or the whole of his property;

11. "Articles of Association" include memorandum of association;

3. **<u>Instruments Chargeable With Stamp Duty</u>**

The following instruments shall be chargeable with stamp duty:

1. Memorandum and articles or Association of any business organization;
2. Award;
3. Bonds;

4. የዕቃ ማከማቻ ማረጋገጫ ሰነድ
5. ውል፣ስምምነትና የእነዚህ መግለጫ
6. የመያዣ ሰነዶች
7. የሕብረት ስምምነት
8. የሥራ /ቅጥር/ ውል
9. የኪራይ፣ የተከራይ አከራይና መሰል መብት የማስተላለፊያ ሰነዶች ጭምር
10. ማረጋገጫ
11. የውክልና ሥልጣን
12. የንብረት ባለቤትነትን ማስመዝገቢያ ሰነድ

4/ <u>የቴምብር ቀረጥ አከፋፈል ልክ</u>

1. በአንቀጽ 3 ስር በተመለከተው በእያንዳንዱ ሰነድ ላይ መከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን ከዚህ ጋር በተያያዘውና የዚህ አዋጅ አንድ አካል ሆኖ በሚቆጠረው ሰንጠረዥ ውስጥ እንደተዘረዘረው ይሆናል።

2. አንድ ሰነድ ለ2ኛ ጊዜ ተፈጻሚ ሲሆን ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን በዚሁ ሰንጠረዥ ውስጥ የተመለከተው ነው።

5/ <u>የቀረጡ አተማመን</u>

1. በአንድ ሰነድ መሠረት ተፈጻሚ የሚሆነው መብት ወይም ግዴታ ሊተመን የሚችል ከሆነ በዚሁ ሰነዱ ላይ የሚከፈለው የቀረጥ መጠን በሰንጠረዥ ላይ እንደተመለከተው የዋጋው መቶኛ ይሆናል።

2. በአንድ ሰነድ መሠረት ተፈጻሚ የሚሆነው መብት ወይም ግዴታ ሊተመን የማይችል ከሆነ በዚሁ ሰነድ ላይ ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን ለእያንዳንዱ ሰነድ በዚሁ ሰንጠረዥ ውስጥ የተመለከተው የቀረጥ መጠን ይሆናል።

3. አንድ ሰነድ ላይ ተከፋይ የሚሆነው ቀረጥ በብር ሳይሆን በሌላ ገንዘብ ከሆነ የቀረጡ መጠን የሚሰላው ሰነዱ በተፈጸመበት ቀን በዋለው የምንዛሪ ልክ ነው።

4. በስቶክ ወይም ሌላ ዋስትና ባለው ነገር

4. Warehouse bond;
5. Contract and agreements and memoranda thereof,
6. Security deeds;
7. Collective agreement;
8. Contract of employment;
9. Lease, including sub-lease and transfer of similar rights;
10. Notarial act
11. Power of attorney;
12. Documents transfering title to property.

4. Rates of Stamp Duty

1. The applicable rates of stamp duty for each instrument mentioned under Article 3 shall be those specified in the schedule attached hereto and constituting and integral part hereof
2. The rate payable at any subsequent execution shall be those specified in the same schedule

5. Mode of Valuation

1. Where the value of the right or obligation executed by means of an instrument can be determined, the rate chargeable on such instrument shall be the precentage of such value to specified in the schedule
2. Where the value of the right or obligation executed by means of an instrument cannot be determined, the amount chargeable on such an instrument is the fixed amount specified for each such instrument in the schedule.
3. Where an instrument is chargeable with stamp duty in respect of any amount expressed in any currency, other than Birr, such amount shall be computed on the basis of the prevailing rate of exchange.
4. Where an instrument is chargeable

ላይ ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን በዋጋው ላይ ተመስርቶ ከሆነ የቀረጡ መጠን የሚሰላው ሰነዱ በተፈጸመበት ቀን በዋለው አማካኝ ዋጋ መሠረት ነው።

5. ብዙ የተለያዩ ነገሮች የተጠቃለሉበት ወይም ለብዙ ልዩ ሰነዶች የቆመ ማናቸውም ሰነድ በያዛቸው ልዩ ልዩ ሰነዶች መጠን በዚህ አዋጅ መሠረት በእያንዳንዱ ሰነድ ላይ የሚከፈለው ቀረጥ በመጠቃለል ተደምሮ ይከፈልበታል።

6. ሀ/ ንብረትን በባለቤትነት ለማስመዝገብ በተቋቋመ ሰነድ ላይ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ የሚተመነው በንብረቱ ሰነድ ውስጥ በተወሰነው የንብረቱ ዋጋ ላይ ሆኖ ዋጋው በገንዘብ ቢሮ ተቀባይነት ያገኘ እንደሆን ነው።

ለ/ በንብረቱ ሰነድ ላይ የተመለከተውን ዋጋ የክልሉ ገንዘብ ቢሮ ያልተቀበለው እንደሆነ ተገቢው የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልበት የንብረቱ ዋጋ ለዚሁ ጉዳይ የክልሉ ገንዘብ ቢሮ በሚሰይመው ኮሚቴ ይወሰናል።

6/ <u>የክፍያ ግዴታ</u>

1. ከዚህ በታች በተመለከቱት ንዑስ አንቀጾች በሌላ አኳኋን ካልተገለጸ በስተቀር በአንድ ሰነድ ተጠቃሚ የሆነ ሰው ሰነዱ ላይ የሚተመነውን የቴምብር ቀረጥ የመክፈል ግዴታ አለበት።
2. በኢትዮጵያ ውስጥ ሰነዱ የሚሰራው ወይም የሚሰጠው ሰው ሰነዱ እንደተፈጸመ የቴምብር ቀረጡን የመክፈል ግዴታ አለበት። ሆኖም አንድ ሰነድ የተሰራው ወይም

with stamp duty on an ad-valorem basis in respect of any stock or of any marketable security, such amount shall be computed on the average value of the stock or security prevailing at the time when the instrument is made.

5. Any instrument comprising or relating to several distinct matters shall be chargeable with the aggregate amount of duties payable in respect of each separate instrument.

6.a) The stamp duty payable on documents transfering title shall be calculated on the value of the property involved as agreed upon between the transferer and the transferee, provided however that such valuation is approved by the Finance Bureau

b) Where the value agreed between the transferer and the transferee is not acceptable to the Finance Bureau the value of the property involvd in the transfer of title shall, for the purpose of calculating the stamp duty, be determined by a special committee which shall be appointed for such purposes by the Regional Finance Bureau

6. **Liability**

1. Unless otherwise provided herein the beneficiary of any instrument shall be liable to pay the stamp duty thereon.

2. The person making drawing or issuing an instrument in Ethiopia shall be liable for the payment of stamp duty provided, however,

የተሰጠው ከኢትዮጵያ ውጭ ከሆነ የቴምብር ቀረጡን የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰነዱን ኢትዮጵያ ውስጥ መጀመሪያ ያስፈጸመው ሰው ነው።

3. በኪራይ ውል ውስጥ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር በኪራይ ውል ላይ የሚከፈለውን የቴምብር ቀረጥ የመክፈል ግዴታ ያለበት ተከራይ ነው።

4. በመያዣ ሰነድ ላይ የሚከፈለውን የቴምብር ቀረጥ ተበዳሪው የመክፈል ግዴታ አለበት።

5. በንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ ሰነድ ላይ ሊከፈል የሚገባውን የቴምብር ቀረጥ ሌላ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የመክፈል ግዴታ ያለበት የንብረቱ ባለቤትነት የሚመዘገብለት ሰው ይሆናል።

6. ውል ወይም ስምምነት የሚመሰርቱ ወገኖች ለቴምብሩ ቀረጥ በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ።

7. በቅጥር ውል ላይ የሚከፈለውን የቴምብር ቀረጥ የመክፈል ግዴታ የአሰሪው ይሆናል።

8. ጉዳያቸውን በግልግል የሚያስወስኑ ወገኖች ለቴምብሩ ቀረጥ አከፋፈል በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ።

9. በኅብረት ስምምነት ላይ ለሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ አሰሪውና ሰራተኞቹ በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ።

7/ <u>ቀረጡ የሚከፈልበት ጊዜና ሁኔታ</u>

1. የቴምብር ቀረጥ የሚከፈለው በሚከተለው ጊዜና ሁኔታ ነው።

ሀ. በመመስረቻና መተዳደሪያ ጽሑፎች ከምዝገባ በፊት ወይም በምዝገባ ጊዜ

ለ. በግልግል ውሳኔው ከመስጠቱ በፊት ወይም በሚሰጥበት ጊዜ

ሐ. በውል ወይም በስምምነት ሰነዶች ላይ ከመፈረማቸው በፊት ወይም በሚፈርሙበት ጊዜ

መ. በኪራይ ወይም በተከራይ አከራይ

that when an instrument is made (drawn) or issued outside Ethiopia the person who is first executing it in Ethiopia shall be liable for the payment of stamp duty.

3. Unless otherwise specified in the lease agreement the stamp duty in respect of the lease agreement shall be paid by the lessee.

4. The borrower shall be liable for the payment of stamp duty chargeable on security deeds.

5. The transferee shall, unless otherwise agreed, be liable for the payment of stamp duty chargeable on documents transfering title to property.

6. Parties to a contract or to an agreement are jointly and severally liable for the payment stamp duty thereon

7. The employer shall be liable for the payment of stamp duty on contracts of employement

8. Parties to an award are jointly and severally liable for the payment of stamp duty thereon

9. The employer and employees are jointly and severally liable for the payment of stamp duty on collective agreement.

7. Time and manner of Payment

1. The stamp duty shall be paid:

a) On memorandum and articles of association, before or at the time of registration;

b) On awards, before or at the time of issuance of the award;

c) On contracts or agreements, before or at the time of signature;

d) On leases or sub-leases before

ውል ላይ ውሉ ከመፈረሙ በፊት ወይም በሚፈረምበት ጊዜ

ሠ. በማረጋገጫ ሰነድ ላይ ማረጋገጫው በሚሰጥበት ጊዜ

ረ. በመያዣ ሰነድ ላይ ከመፈረሙ በፊት ወይም በሚፈረምበት ጊዜ

ሰ. በንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ ሰነድ ላይ የማስመዝገቡ ተግባር ከመፈጸሙ በፊት ወይም በሚፈጸምበት ጊዜ

2.ሀ. የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ ከብር 50 በታች በሚሆንበት ጊዜ ክፍያው ተገቢውን ዋጋ የያዘውን ቴምብር በመለጠፍ ይፈጸማል።

ለ. የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ ከብር 50 የበለጠ ሲሆን ወይም የሰነዱ ዓይነትና ሁኔታ ለየት ያለ አሠራርን ሲጠይቅ ገንዘብ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ቴምብር ከመለጠፍ በሌላ መንገድ ቀረጡ እንዲከፈል ሊያደርግ ይችላል።

3. ሀ. የቀረጥ ቴምብር በተለጠፈበት ሰነድ የሚሰራ ወይም የሚቀበል ሰው በዚህ ቴምብር ሁለተኛ እንዳይሰራ መሠረዝ አለበት።

ለ. ቴምብር የተለጠፈበትን ሰነድ የሚቀበሉ ሰዎች ስለቴምብሩ አሰራረዝ ገንዘብ ቢሮ በሚወስነው መሠረት ይፈጽማሉ።

ሐ. በሰነድ ላይ የተለጠፈ ቴምብር ገንዘብ ቢሮ በሚወስነው መሠረት ካልተሰረዘ ሰነዱ ቴምብር እንዳልተለጠፈበት ይቆጠራል። በዚህ ምክንያት የሚመጣው ኃላፊነት የሚወድቀው በባለጉዳዩ ላይ ሳይሆን የቀረጥ ቴምብር በተለጠፈበት ሰነድ በሚሰጥ ወይም በሚቀበል ሰው ላይ ይሆናል።

8/ <u>የአማራ ብሔራዊ ክልል ገንዘብ ቢሮ ሥልጣን</u>

የክልሉ ገንዘብ ቢሮ፤

or at the time of signature;

e) On notarial acts, at the time of issuance;

f) On security deeds, before or at the time of signature;

g) On documents transfering title to property, before or at the time the transfer effected;

2. a) The payment of a stamp duty under Birr fifty (50) shall be effected by affixing stamp of appropriate value to the instrument.

b) When the stamp duty exceeds Birr fifity (50) or where the type and nature of instrument so requires, the Federal Revenue Board may by directive provide that stamp duty paid by means other than affixing stamp.

3. a) Whoever executes an instrument bearing an adhesive stamp shall at the time execution cancel the same, so that it cannot be used again.

b) Persons required to cancel the adhesive stamp shall cancel it in such manner as will be prescribed by the Regional Finance Bureau

c) Any instrument bearing an adhesive stamp which has not been cancelled as prescribed by the Regional Finance Bureau shall be deemed, so far as such stamp is concerned to be unstamped.

8. Power of the Amhara National Regional State Finance Bureau

The Amhara National Regional State

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የተወሰነውን ቀረጥ ለመሰብሰብና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም፤
2. ቀረጥ ከፋዩች ስለቀረጡ አወሳሰን የሚረዱ መዛግብትንና ደብተሮችን ወረቀቶችን ማንኛውንም ልዩ ልዩ ሰነዶችንና ውሣኔዎች እንዲያቀርቡ ለማድረግና ለመመርመር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ራሱ ቀርቦ እንዲያስመረምር ወይም እንዲያስረዳ ለማዘዝ፤
3. ጉዳዩ የሚመለከተው ቀረጥ ከፋይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ በተመለከተው መሠረት ለመፈጸም ፈቃደኛ ሳይሆን በቀረ ጊዜ ቀረጡን በግምት ለመወሰንና ለመሰብሰብ፤ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

9/ ይግባኝ የማቅረብ መብት

የገንዘብ ቢሮ በወሰነው የቴምብር ቀረጥ ሂሣብ የማይስማማ ቀረጥ ከፋይ ቢሮው ውሳኔውን በጽሑፍ ካስታወቀበት ቀን እንስቶ ከ21 ቀኖች በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል።

10/ የቴምብር ቀረጥ አለመከፈል የሚያስከትለው ውጤት

1. ማንኛውም ሰነድ በዚህ አዋጅ መሠረት ትክክለኛ የቴምብር ቀረጥ ካልተከፈለበት በስተቀር በውል ወይም በሕግ ማስረጃ የመቀበል ሥልጣን ባለው ሰው ወይም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ዘንድ በማስረጃነት ተቀባይነት አይኖረውም፤ ምልክት አይደረግበትም ወይም ማረጋገጫ አይሰጥበትም።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀስ /1/ የተደነገገው በወንጀል ፍርድ ቤት በሚታይ ክርክር በማስረጃነት የሚቀርቡ ሰነዶችን አይመለከትም።

Finance Burea

1. Collect the stamp duty determined under, and implement the provisions of this Proclamation
2. Require persons liable to pay stamp duty to submit for its inspection any registers, books, papers, documents and proceedings necessary for the determination of stamp duty, or where necessary to require the attendance of such persons who shall give the necessary explanation in the course of its inspection of such records.
3. To determine by estimation the stamp duty payable under this Proclamation if the concerned person fails to comply with its requests provided in sub-article 2 of this Article.

9. **Right to Appeal**

Persons dissatisfied with the decision of Finance Bureau in respect of the amount of stamp duty may, within 21 days from the date of notification of the decision rendered in writing, make an appeal against the decision to the High Court.

10. **Effect of Non-Payment of Stamp Duty**

1. No instrument chargeable with stamp duty shall be admitted in evidence for any purpose by any person having by law or consent of parties authority to receive evidence or shall be noted upon or authenticated by any such person or public office, unless such instrument is duly stamped.
2. Sub-article 1 of this Article shall not affect the validity of the instrument when submitted as evidence in any proceedings in a criminal court.

3. በዚህ አዋጅ መሠረት በመረጃነት ተቀባይነት ያላገኙ ሰነዶች ሊከፈልባቸው የሚገባው ቀረጥ በሁለት እጥፍ ተከፍሎባቸው በመረጃነት ሊቀርቡ ይችላሉ፤ ሆኖም በዚህ ሁኔታ የሚከፈለው ቀረጥ ከ10 ብር ማነስ የለበትም።

4. ከዚህ በላይ በተመለከቱት ንዑስ አንቀጾች የተወሰነው ቅጣት ተፈፃሚ መሆን በዚህ አዋጅ አንቀፅ 12 መሠረት ከመክሰስ አያግድም።

11/ <u>ከቀረጥ ነፃ መሆን</u>

የክልሉ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 18/1989 ተፈፃሚ የሚሆንባቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከቴምብር ቀረጥ ክፍያ ነፃ ናቸው።

12/ <u>ቅጣት</u>

1. ማንኛውም ሰው፤

ሀ. ማናቸውንም ቀረጥ ሊከፈልበት የሚገባውን ሰነድ ተገቢው ቴምብር ሳይለጠፍበት ያስፈፀመ ወይም ከምስክርነት በስተቀር የፈረመ እንደሆነ፣

ለ. ተገቢውን ቀረጥ እንዳይከፍል ለማድረግ በማሰብ የአንድን ሰነድ እውነተኛ ሁኔታ የደበቀ እንደሆነ፤ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ በፌደራሉ መንግሥት የቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 110/1990 አንቀጽ 12(1) መሠረት ከብር 25000 (ሃያ አምስት ሺህ ብር) በማያንስና ከብር 35000(ሰላሳ አምስት ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮና ከአሥር ዓመት በማያንስና ከአስራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

2. ማንኛውም ሰው፣

ሀ. ቴምብር ወይም ቴምብር የተለጠፈበት ወረቀት ለመሸጥ ተፈቅዶለት በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን የጣሰ እንደሆነ ወይም

3. Any instrument inadmissible in accordance with this Proclamation shall be admitted in evidence on Payment of two times the amount due which shall not be less than 10 Birr.

4. The application of any penalty pursuant to the foregoing Articles shall not bar the prosecution of any person in accordance with Article 12 of this Proclamation.

11. **Exemption**

Public bodies on which the Amhara National Regional State Financial Administration Proclamation No. 18/1997 applies shall be exempt from payment of stamp duties.

12. **Penalty**

1. Any Person

a) executing a document chargeable with stamp duty without the same being stamped, other than as a witness,

b) shall be liable on conviction in accordance with the Federal Government Stamp duty Proclamation No. 110/1998 Article 12(1) to fine not less than birr 25,000 and not more than birr 35,000 and to reqorous imprisonment for a term of not less than 10 and not more than 15 years.

2. Any person

a) appointed to sell stamp or stamped paper who disobeys regulations issued under this Proclamation; or

ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ በፌደራሉ መንግሥት የቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 110/1990 አንቀፅ 12(2) መሠረት ከብር 5000 (አምስት ሺህ ብር) በማያንስና ከብር 20000 (ሃያ ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫና ከአምስት ዓመት በማያንስና ከአስር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

13/ <u>በሥራ ላይ የማይውል ሕግ</u>

የቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 334/1979 ዓ.ም. ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በአማራ ክልል ተፈፃሚነት አይኖረውም።

14/ <u>ደንብና መመሪያ</u>

ይህን አዋጅ የማሻሻል ሥልጣን የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ሆኖ፤

1. የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ለአዋጁ አፈፃፀም የሚረዳ ደንብና መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

2. የገንዘብ ቢሮ ለአዋጁ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን የማውጣት ስልጣን ተሰጥቶታል።

15/ <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት

ኅዳር 10 ቀን/1991 ዓ.ም.

ባህር ዳር

shall be liable on conviction in accordance with the Federal Government stamp duty Proclamation No. 110/1998 Article 12(2) to fine not less than Birr 5,000 and not more than birr 20,000 and to rigorous improsnment for a term of not less than 5 years and not more than 10 years.

13. Repeal

The stamp Duty Proclamation No. 334/1987 is hereby repealed and replaced by this Proclamation.

14. Directives

In addition to the power of the Council to revise this Proclamation

1. The Regional Executive Committee may issue regulation for the proper implementation of this proclamation.
2. Directives for the proper implementation of this proclamation may be issued by the Finance Bureau

15. Effective Date

This Proclamation shall come into force on the date of its ratification by the Coural of the Amhara National Regional State

Done at Bahir Dar

This 19 th day of November ,1998

The Council Of The Amhara National Regional State

የቴምብር ቀረጥ ታሪፍ ሰንጠረዥ

በሰነዶች ላይ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ የሚወሰነው፣ የሚጠየቀውና የሚሰበሰበው ከዚህ በታች በተመለከተው ልክ ነው።

ተ.ቁ	የሰነዱ ዓይነት	የተወሰደ ስሌት መሠረት	የማስከፈያ ልክ
1	የማንኛውም የንግድ ሥራ ወይም ከታች በተራ ቁጥር 2 በተመለከቱት ውጭ የሆነ ማናቸውም ሌላ ማኅበር የተመሠረተበት መተዳደሪያ ደንብ፤ ሀ. መጀመሪያ ሲፈፀም ለ.በመለጠቅ ሲፈፀም	 በቁርጥ በቁርጥ	 ብር 350.00 ብር 350.00
2	የኅብረት ሥራ ማኅበርወይም የብዙኃን ማህበራት ወይም የሙያ ማህበራት መተዳደሪያ ደንብ፤ ሀ. መጀመሪያ ሲፈፀም ለ.በመለጠቅ ሲፈፀም	 በቁርጥ በቁርጥ	 ብር 35.00 ብር 10.00
3	ግልግል	በዋጋው	የሚተማመን 1% የማይተማመን 1%
4	ማገቻ(ቦንድ)	በዋጋው	1%
5	የዕቃ ማከማቻ ማረጋገ ሰነድ	በዋጋው	1%
6	ውሎች ፤ስምምነቶችና መግለጫዎቻቸው	በቁርጥ	ብር 5.00
7	የመያዣ ሰነድ	በዋጋው	1%
8	የሕብረት ስምምነት ሀ.ሲመዘገብ ለ.ሲሻሻል	 በቁጥር በቁርጥ	 ብር 350.00 ብር 100.
9	የቅጥር ውል ስምምነት	የአንድ ወር ደመወዝ	1%
10	ኪራይ የተከራይ አከራይና መሰል ሙብት ማስተላለፊያ ሰነድ	በዋጋው	1%
11	ማረጋገጫ	በቁርጥ	ብር 5.00
12	የውክልና ሥጣን	በቁርጥ	ብር 35.00
13	የንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ	በዋጋው	2%

SCHEDULE OF STAMP DUTY RATES

The stamp duty on each instrument shall be charged, levied and collected at the following rates.

No	Insturments chargeable with stamp duty	Basis of valuation	Rates of stamp Duty
1	Memorandum and Articles of Assiocation of any business organizztions, exlcuding what is mentioned below under № 2 a. upon 1st execution b. upon any subsequent execution	 flat flat	 Birr 350.00 " 100.00
2	memorandm and Articles of Association of cooperation or mass or proffessional organization a. upon 1st execution b. upon any sabsequent execution	 flat flat	 Birr 35.00 " 10.00
4	Bonds	"	1%
5	Warehouse Bond	"	1%
6	Contracts and agreements and memeoranda thereof	flat	Birr 5.00
7	Security deeds	one value	1%
8	collective Agreement A. on 1st execution B. on any subsequent execution	 flat flat	 Birr 350.00 " 100.00
9	Contract of employment	salary	1%
10	Lease including sub-lease and transfer therof	one value	0.5%
11	Notaril act	flat	Birr 5.00
12	Power of Attomey	flat	Birr35.00
13	Register	one value	2%